አምሳ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፰
54th year — No. 8

አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ. ም.
Addis Ababa, 15th February 1995

ጠበቃ ምንዳ ግርማ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

ነጋሪት ጋዜጣ

NEGARIT GAZETA

OF THE TRANSITIONAL GOVERNMENT OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ 1.30 Unit Price	በኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የተወካዮች ምክር ቤት ተጠባቂነት የወጣ	የፖስታ ማተን ቁ. ፹ሺ፩ (80,001)

ግ ው ጌ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲/፲፱፻፹፯ ዓ. ም.

ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች የወጣ አዋጅ . . . . . ገጽ ፭፻፵፬

CONTENTS

Proclamation No. 110/1995

Review of Properties Taken in Violation of the Relevant Proclamations Proclamation . . . . . Page 144

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲/፲፱፻፹፯

ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች የወጣ አዋጅ

በአለፈው መንግሥት ወታደራዊ አስተዳደር ዶርግ ፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፣ በአብዮትና ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ ፣ በከተማና በቀበሌ ገበሬ ማኅበራት እና በሌሎች መን ግሥታዊና ሕዝባዊ ድርጅቶች ወይም ኃላፊዎች ከአዋጅ ውጭ በመመሪያ፣በቀላጤና በቃል ትእዛዝ የተወሰዱ ንብረቶች ለሕጋዊ ባለቤታቸው እንዲመለሱ የኢትዮጵያ የሽግግር መን ግሥት የሚያምንበት በመሆኑ ፤

ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን አጣርቶ እንዘህ ንብረቶች ለሕጋዊ ባለቤቶቻቸው የሚመለሱበት ሁኔታ መልኩ ሳያገኝ በመቆየቱና በመሳሰሉት ምክንያቶች አፈጻጸሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ የተወሳሰበ ችግሮች እየተፈጠሩ በመምጣታቸው የመብት ጥያቄዎች ላይ አፋጣኝና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ውሣኔ የሚሰጥ መንግሥታዊ አካል መሰየም በማስፈለጉ፣

በሕገመንግሥት ጉባኤ የመሸጋገሪያ ውሣኔ መሠረት የሚከተለው ታውጇአል ።

፩. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ «ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች የወጣ አዋጅ ቁጥር ፭፻፲/፲፱፻፹፯» ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

Proclamation No. 110/1995

A PROCLAMATION RELATING TO PROPERTIES TAKEN IN VIOLATION OF THE RELEVANT PROCLAMATIONS

WHEREAS, the Transitional Government of Ethiopia believes that properties taken pursuant to directives, written and oral orders issued in violation of the relevant proclamations by the defunct Military Administrative Council, the Council of Ministers, Revolutionary Operations Coordinating Committees, Urban Dwellers' and Peasant Associations, other governmental and mass organizations and their officials should be returned to their rightful owners;

WHEREAS, the delay in ascertaining properties taken in violation of the relevant proclamations and in resolving the issue of returning such properties to their rightful owners and other similar causes have, through time, created complex problems of implementation, and it has now become necessary to designate a governmental body with the authority to make prompt and effective decision on claims of title;

NOW, THEREFORE, in accordance with the Resolution on the Transition, of the Constituent Assembly, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Review of Properties Taken in Violation of the Relevant Proclamations Proclamation No. 110/1995."

ጠበቃ ምንዳ ግርማ

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ፣

፩. «ኤጀንሲ» ማለት በኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፹፮ የተቋቋመው ኤጀንሲ ነው ፣

፪. «ቦርድ» ማለት የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ነው ፣

፫. «ከአዋጅ ውጭ የተወሰደ ንብረት» ማለት የሃብት ማፍሪያ መሣሪያዎችን ወደ መንግሥት ለማዛወርና በቁጥጥሩም ሥር ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፭፮/፲፱፻፷፭ ዓ/ም ፣ የገጠርን መሬት የሕዝብ ሃብት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፩/፲፱፻፷፭ ዓ/ም ፣ የከተማን ቦታና ትርፍ ቤት የመንግሥት ንብረት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፵፯/፲፱፻፷፭ ዓ/ም እና የግል ትምህርት ቤቶችን የሕዝብ ሃብት ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር ፶፬/፲፱፻፷፮ ዓ/ም ካተደነገገው ውጭ በመመሪያ ፣ በቀላጤና በቃል ትእዛዝ የተወሰደ ንብረት ማለት ነው ።

፫. የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፫ በተመለከቱትና በመንግሥት እጅ በሚገኙ ንብረቶች ላይ ይሆናል ።

፬. ስለኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

፩. ኤጀንሲው በኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፹፮ ዓ/ም ከተሰጠው ሥልጣን በተጨማሪ ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን የባለቤትነት ሁኔታዎች እንዲያጣራና እንዲወሰን ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፣

ሀ) ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ የሚቀርቡ የመብት ጥያቄዎችን ይመዘግባል ፣

ለ) የቀረቡለትን ያመብት ጥያቄዎችና ሁኔታዎች በአዋጆቹ መሠረት ይመረምራል ፣ ለምርመራው አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን ከማናቸውም የመንግሥት ወይም የግል መሥሪያ ቤት ፣ ድርጅት ወይም ተቋም እንዲሁም ከማንኛውም ግለሰብ ለማግኘት ፣ የምስክር ቃል ለመቀበል ወይም የጽሑፍ ማስረጃ እንዲያቀርብለት ለማዘዝ ይችላል ፣

ሐ) ከአዋጅ ውጭ የተወሰደን ንብረት ባለቤትነት በተመለከተ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ መረጃዎችን እያጣራ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል ውሳኔው እንዲፈጸም አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል ፣

2. *Definitions*

In this Proclamation:

1. "Agency" means the Ethiopian Privatization Agency established by the Ethiopian Privatization Agency Establishment Proclamation No. 87/1994;

2. "Board" means the Board of Management of the Agency;

3. "Property taken in violation of the relevant proclamation" means any property taken pursuant to directives, written or oral orders given in violation of the Government Ownership and Control of the Means of Production Proclamation No. 26/1975, the Public Ownership of Rural Lands Proclamation No. 31/1975, the Government Ownership of Urban Lands and Extra Houses Proclamation No. 47/1975 and the Public Ownership of Private Schools Proclamation No. 54/1976.

3. *Scope of Application*

This Proclamation shall only apply to property as defined under sub-article 3 of Article 2 of this Proclamation which is under the physical possession of the Government.

4. *Powers and Duties of the Agency*

1. The Agency shall, in addition to the powers and duties vested in it under the Ethiopian Privatization Agency Establishment Proclamation No. 87/1994, have the power to investigate and decide on claims of ownership in respect of property taken in violation of the relevant proclamations.

2. Without limiting the generality stipulated in sub-article 1 of this Article, the Agency shall have the following powers and duties;

a) to register claims of title presented to it in respect of property taken in violation of the relevant proclamations;

b) to investigate on the basis of the relevant proclamations the claims and conditions of title submitted to it; to obtain from any governmental or private office, organization or establishment as well as from any private person any evidence it deems necessary for such investigation; to hear the testmony of witnesses and to require the production before it of any written evidence;

c) to give appropriate decisions on claims in respect of property taken in violation of the relevant proclamations upon examination of the evidence therefore; and to take the measures necessary for the implementation of same;

መ) አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣንና ተግባሩን ከዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ጋር አግባብ ላለው የክልልና የማዕከላዊ የመንግሥት አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል ፣

ሠ) የመብት ጥያቄዎች ከመረጃ ማጣራት አልፎ የፖሊሲ ጥያቄ ወይም ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ሃሣብ ያቀርባል ፣

ረ) ሥልጣንና ተግባሩን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል ።

፭. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር

ቦርዱ በኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፹፯/፲፱፻፹፯ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በተጨማሪ ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን በተመለከተ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፤

፩. ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተዘረዘሩትን ሥልጣንና ተግባሮች ለማስፈጸም ዝርዝር ሥራዎችን ያወጣል ፣

፪. የባለቤትነት ጥያቄዎችን በተመለከተ ተጨማሪ የፖሊሲ ውሣኔ ወይም ሕግ ያስፈልጋል ብሎ ሲያምን አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ሃሣብ ያቀርባል ፣ የፖሊሲ ውሣኔ ከተደረገ ወይም ሕግ ከጸደቀ በፖሊሲውና በሕጉ መሠረት ያስፈጽማል ፣

፫. የባለቤትነት ጥያቄን በሚመለከት በማንኛውም የኤጀንሲው አካል በሚሰጠው ውሣኔ ላይ በሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ ይሰጣል ።

፮. ተጨማሪ የቦርድ አባላትን ስለመሾም

ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን በሚመለከት ተጨማሪ ቋሚ የቦርድ አባላት በመንግሥት ይሾማሉ ።

፯. የመተባበር ግዴታ

ማናቸውም የመንግሥት ወይም የግል መሥሪያ ቤት ድርጅት ወይም ተቋም ወይም ማንኛውም ግለሰብ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት ።

፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

፩. ይህ አዋጅ በጸናበት ቀን ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን በሚመለከት በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያሉ ክሶች ወይም የአፈጻጸም ጉዳዮች በኤጀንሲው አማካይነት ተገቢውን ውሣኔ ያገኛሉ ።

፪. ኤጀንሲው ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በኦስተዳደራዊ ውሣኔ ከአዋጅ ውጭ በተወሰዱ ንብረቶች ላይ የተሰጡ ውሣኔዎችን በተመለከተ የውሣኔዎችን አግባብነት በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት ይችላል ።

፫. ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በፊት በጉዳዩ የሥረ ነገር ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ታይቶ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሲቀርብለት እንደገና የማየት ሥልጣን ይኖረዋል ።

d) to delegate its powers and duties with detailed implementation guidelines, as it deems it necessary, to the appropriate regional and central government organs;

e) to submit to the appropriate government organ proposals regarding claims of title where it finds that they require, beyond examination of evidence, policy or legal determination;

f) to carryout such other activities as are necessary for the accomplishment of its powers and duties.

5. *Powers and Duties of The Board*

The Board shall, in addition to the powers and duties vested in it under the Ethiopian Privatization Agency Establishment Proclamation No. 87/1994, have the following powers and duties in respect of properties taken in violation of the relevant proclamations:

1. the Board shall issue detailed directives for the purpose of executing the powers and duties specified under Article 3 of this Proclamations;

2. it shall submit to the appropriate government organ proposals regarding the settlement of claims of title where it believes that additional policy decision or law is necessary; and, upon the adoption of policy or issuance of law, it shall implement such policy and law;

3. it shall decide on petitions which are submitted to it against decisions regarding claims of title given by any organ of the Agency.

6. *Appointment of Additional Board Members*

Additional permanent Board members for the aspect of the powers and duties of the Board relating to property taken in violation of the relevant proclamations shall be appointed by the Government.

7. *Duty to Cooperate*

Any government or private office, organization or institution or individual shall have the duty to cooperate in matters relating to the implementation of this Proclamation.

8. *Transitiocnal Provisions*

1. Any case which, on the effective date of this Proclamation, is pending before any court or is under execution preccedings ssall get the appropriate decision by the Agency.

2. The Agency shall have the power to review the property of any administrative decisions regarding property taken in violation of the relevant proclamations given proir to the effective date of this Proclamation and to give proper decision thereon.

3. The Central High Court shall, upon complaint, have jurisdiction to review and decide on any case involving property taken in violation of the relevant Proclamations, decided on by any court having no jurisdiction on the subject-matter of the case.

፱. ከሌሎች ሕጐች ጋር ስላለው ቅራኔ

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፲. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፰ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ. ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት

ፕሬዚዳንት

9. *Conflict With Other Laws*

No law which is inconsistent with this Proclamation shall have force or effect in respect of matters provided for in this Proclamation.

10. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa this 15th day of February 1995

MELES ZENAWI

PRESIDENT OF THE TRANSITIONAL

GOVERNMENT OF ETHIOPIA

ጠበቃ ምንዳ ግርማ

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ።
Berhanena Selam Printing Enterprise